# ለእግዚአብሔር ፍቅር

**ጥር** 1994 **Januaru 2002**

ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ÷የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል። (ትንቢተ ኢሳይያስ 54÷13)

"እግዚአብሔር ሆይ!አንተን ማመስገን÷ልዑል ሆይ ! ስለ ክብርህ መዘመር እንዴት መልካም ነው ! ስለ ዘላለማዊ ፍቅ ርህ በየማለዳው መናገር ÷ ስለ እውነትነትህ በየሌሊቱ ማው ራት ÷ እንዴት መልካም ነው! ባለ አውታር በሆኑ የሙዚቃ መሣርያዎችና በበገና ቅኝት ÷ አንተን ማመስገን እንዴት መልካም ነው ! እግዚአብሔር ሆይ ! የአንተ ታላላቅ ሥራ ዎች ደስ ያሰኙኛል፤ አንተ ስላደረግሃቸውም ነገሮች በደስታ አዘምራለሁ ። እግዚአብሔር ሆይ ! ሥራህ እንዴት ታላቅ ነው! አሳብህስ እንዴት ጥልቅ ነው! ሰነፍ ሰው ሊያውቀው÷ ሞኝም ሊያስተውለው አይችልም። (መዝሙረ ዳዊት 92÷1-6 አዲሱ ትርጉም)

"ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ÷ <u>የበለስ ዛፍ</u> ምሳሌ ትምሕርት ይሁናችሁ ፤ ቅርንጫፎችዋ ሲያቆጠቁጡና ቅጠሎችዋም ሲለመልሙ ያን ጊዜ ጸደይ መቅረቡን ታውቃላችሁ። እንዲሁም እናንተ ይህን ሁሉ ስታዩ ÷ የሰው ልጅ የሚመጣበት ጊዜ እንደቀረበ እወቁ ። ... ሰማይና ምድር ያልፋሉ ፤ ቃሌ ግን ለዘላለም ይኖራል።" (የማቴዎስ ወንጌል 24÷ 32 ÷ 33 ÷ 35 አዲሱ ትርጉም )

በዚህ ክፍል ጌታ በ<u>በለስ ዛፍ</u> የመሰላት የእግሮቹ ማረፍያ እንድትሆን የተመረጠችውን የዳዊትን ከተማ <u>ጽዮንን</u> ነው ። ወገኖቼ ÷ እግዚአብሔር እስራኤልን እንደ ተስፋ ቃሉ ከአ ራቱ ማዕዘናት (ከኢትዮጵያችንም) እየሰበሰበ ማደራጀቱን እንደሚያፋጥን ከዓለም ዜና ታስተውላላችሁ ? እግዚአ ብሔር ለአይሁድና ለወዳጆቿ የሚያሳየው ሞገስ ጠላቶቿን በቅናት እንዳነሣሣ ልብ ትላላችሁ? እንግድያው <u>"... ይህን ሁሉ ስታዩ ÷ የሰው ልጅ የሚመጣበት ጊዜ እንደ ቀረበ እወቁ ።"</u> ለክብሩ እንድናደርግ ጌታ በልባችን ያስቀመ ጠውን ሁሉ በቶሎ እናድርግ ። ይህንን በማሰብ :-

**በዚህ አዲስ ዓመትና በቀረው ዘመን :- "እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ፤በሕይወትህ ዘመ ን ሁሉ÷የእየሩሳሌምን መልካምነትዋን ታያለህ ። የልጆችህንም ልጆች ታያለህ። በእስራኤል ሰላም ይሁን።" "እግዚአብሔር ይባርክህ÷ይጠብቅህም:- እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ÷ ይራራልህም ፤ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ÷ሰላሙንም ይስጥህ።"** (መዝሙረ ዳዊት 128÷5) (ዘኊልቁ 6÷24)

**ብሩክ *ዓመት* !**

**ከእግዚአብሔር ፍቅር የወንጌል አገልግሎት :-**
.

መላኩ÷ዓለምና ሊበን ትዕዛዙ ።

**አድራሻችን :-** God's Love
PO Box 6734
Lee's Summit MO 64064
E-mail mtizazu@hotmail.com
Fax 816-246-9395

# ጓደኛ (ወዳጅ)

"ዳዊትም ለሳኦል መናገሩን በፈጸመ ጊዜ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች÷ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደው።" (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 18÷1)

"ዮናታንም ዳዊትን:- ነፍስህ የወደደችውን ሁሉ አደርግልሃለሁ አለው።" (መ.ሳሙኤል ቀዳማዊ 20÷4)

ጊዜው የኢኮኖሚ ቀውስ (ሪሴሽን) ወይም ሐገራዊ የኢኮኖሚ መናጋት በአሜሪካ የተከሰተበት ወቅት ነበረ። እንዲህ ባለ ጊዜ ታላላቅ ትርፎችን በማስገኘት የከበሩና የተመሰገኑ ኩባኒያዎች ዕዳ በዕዳ በመሆን ይከስራሉ።

ይህ ክፉ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ፍቅርና መግባባት የነበራቸው አቶ ማርሊና አቶ ሮበርት የሚባሉ ጓደኛሞች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በንግዱ ዓለም እጅግ የሚስማማሙና እንደ መንታ ልጆች የሚጣጣሙ ጥሩ ወዳጆች ነበሩ። ስለዚህ አንዱ የንግድ ውሳኔ ማድረግ ከብዶት ወይም በሌላ ጉዳይ ተወጥሮ የጨነቀው ዕለት ወደ ሌላኛው ሄዶ የልቡን ሸክም በማካፈል ይጽናና ነበር።

አቶ ማርሊ በዚያ የኢኮኖሚ ቀውስ ወቅት እጅግ ብዙ ገንዘብ በኪሳራ ለማጣት በቃ። ከደረሰበትም ጭንቀት የተነሣ ወደ ወዳ ጁ አቶ ሮበርት ሄደና አጫወተው። አቶ ማርሊ ብሶቱን ተናግሮ ለመጨረስ ሁለት ሰዓት ያህል ፈጀ። የአቶ ማርሊ ወዳጅ አቶ ሮበርትም የወዳጁን ንግግር በትዕግስት ሳያቋርጥና ምክር ለመስ ጠት ሳይቸኩል ያዳምጥ ነበር። አቶ ማርሊም ንግግሩን ከፈፀመ በኋላ ከጓደኛው የሚመጣውን መልስና ምክር ለማዳመጥ በጉጉት ይጠባበቅ ጀመር።

ዳሩ ግን የአቶ ሮበርት መልስና ምክር አጭር ነበረ። እርሱም <u>"ለዚህ ችግርህ የሚሆን መፍትሄ አላውቅም። ነገር ግን አንድ ነገር አውቃለሁ። ያለኝን ተካፍለን ይህን ክፉ ጊዜ አብረን እናሳ ልፋለን እንጂ እኔ በልቼ አድሬ አንተና ቤተሰብህ ጾማችሁን አታድሩም።"</u> የሚል ነበር።

አቶ ማርሊ ይህን በሰማ ጊዜ በቃላት በማይገለጽ መጽናናት ተሞላ። የወዳጁ ከጎኑ መቆም ተስፋ ፡ የአእምሮውን መብራት ለኮሰለት። ወድያውም አስገራሚ የንግድ ራዕዮችን ማስተዋል ጀመረ። የሚያስደንቁ ብሩህ ውሳኔዎችንም በማድረግ ኩባኒ ያውን ከኪሳራ ለማዳንና ያንን ክፉ ወቅት ለማለፍ ቻለ።

አይገርምም? አቶ ማርሊ ችግሩን የተወጣው ከወዳጁ የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ርዳታ በመቀበል አይደለም። ተስፋ በማግኘት ነው። ተስፋም ጭንቀት ያጨለመውን አእምሮውን አበራለት። ችግሩንም ያሸነፈው በብሩህ አእምሮው አስተዋይ ውሳኔዎችን በማድረግ ነው። ቃሉ በ (1ቆሮ 13÷13) እንደሚል :-

"እንዲህም ከሆነ ÷ እምነት ፡ **ተስፋ** ፡ ፍቅር ፡ እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።"

## የቅርብ ወዳጅ (የልብ ጓደኛ) አለህ?

አልፎ አልፎ ምሣ የምትገባበዙትን ማለቴ አይደለም። አንዳ ንዴ ስልክ የምትደዋወሉትንም አይደለም። ባመቸ ጊዜ ተገናኝ ታችሁ የምትጸልዩትንም ሳይሆን በዕውነት የሚቀርብህ ወዳጅ አለህ ? ተማሪ በነበርክበት ጊዜ የነበረህ ዓይነት÷ ከእርሱ የም ትደብቀው የሌለህ ÷ እርሱም የሚደብቅህ የሌለው? ብትስቅ ቀላል÷ ብታለቅስ ደካማ የማይልህ:- ሲሳካልህ ጎሽ÷ ሲበላሽብህ አይዞህ የሚልህ? ስታጠፋ የሚገስጽህ ÷ ሲከፋህ የሚያጽናናህ ? ቢቸግረው የማትጨክንበት÷ ቢጎድልብህ ሳያቅማማ የሚሞላልህ ወዳጅ አለህ? በአጭሩ የጨነቀህ ቀን መጠጊያ የሚሆንህና አንተም የምትሆነው ወዳጅ አለህ ?

ለመሆኑ እንደዚህ ያሉ ጓደኞች በዚህ ዘመን ወዴት ናቸው? በወጣትነት ዘመን እንደነበሩን ያሉ ጠሊቅ ጓደኝነቶች በጉልምስ ና ዘመን ማግኘት የሚያስቸግረው ለምንድን ነው? መልሱን ለሁላችን መተው ይሻላል።

ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ ወዳጅ (ጓደኛ) ያስፈልገዋል። የኑሮ ስኪት ያሰከረውም፡ሸንፈት ያደቀቀውም የቅርብ ጓደኛ ሊኖራቸ ው ይገባል። <u>ያውም ለወንድ ክርስቲያን ወንድ÷ ለሴትም ሴት÷ ጓደኛ ያስፈልጋቸዋል</u>። ምክንያቱም እንዲህ ያለ ቅርብ ጓደኝነ ት በተቃራኒ ጾታ መሐከል (ከትዳር ውጭ) ጤነኛ ሆኖ ሲቀጥል አይታይም።

በአቅመ አዳም ዕድሜ አብዛኛው ሰው ያለውና ጓደኛ የሚላቸ ው÷ በሥራ ቦታ አብረውት የሚውሉትንና የሥራ ሁኔታ ያፈራ ውን መተዋወቅ ነው። ይሁን እንጂ የሥራ ቅርርብ አብዛኛውን ጊዜ የጠበቀ ወዳጅነት ሲፈጥር አይታይም።

አብዛኛው ሰው የዕውነተኛ ጓደኛ ኪሳራ ያጠቃው ነው። የቅ ርብ ወዳጅ ፈልጎ ማግኘትም÷ ማዳበርም÷ አያውቅም። ራሱም ለሌሎች ጥሩ ወዳጅ መሆን እንዳለበት አያውቅም። ከብዙ ሕዝ ብ ጋር ይተዋወቃል። ነገር ግን የልብ ጓደኛ በማጣት በብቸኝነት የተቀጣ ሕይወት ይኖራል። <u>የቅርብ ጓደኛ የሌላቸው ወይም ከቅርብ ወዳጆቻቸው በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነጠሉ ሰዎች (ዲፕሬሽን) ለሚባለውና ለሌሎችም የአእምሮ ሕመሞች በቀላሉ የተጋለጡ መሆናቸውን የሕክምና ባለሙያዎች ይመሰክራሉ ። ሰዎች ነፍሳቸውን በገዛ ራሳቸው የሚያጠፉት በእነዚህ ሁኔታዎ ችና በመሳሰሉት ምንያት ነው።</u>

ጥሩ ጓደኛ ማግኘትም ሆነ ጓደኝነትን ማጽናት ዋጋ ያስከፍላ ል። ከህደት÷መዋረድ÷መቆሳሰል የተለመዱ ናቸው። ነገር ግን የጓደኝነትን ጥበብ ተግተን ብንማርና ብናስተውል ታማኝ ወዳ

ጅ ማግኘት ብዙ ወርቅና ብር ከማግኘት የተሻለ ሆኖ እናገኘዋለን።

ምናልባት ከአንድ በላይ ጓደኛ ይኖረሃል። ወይም አንድም የቅርብ ወዳጅ የለህም። ምናልባት ከብዙ ሰው ጋር ጥሩ ትውውቅ አለህ። ሆኖም የአንዳቸውም ወዳጅነት ተፈትኖ የታወቀ አይደለም። ምናልባት የጓደኛን ጥቅም በአግባቡ ስላልተረዳህ በቂ ጥንቃቄና ርምጃ ወስደህ አታውቅም። የሚከተሉት መጠይቆች በዚህ አኳያ የሚረዱ ናቸው :-

1. ሲከፋህና የልብህን የምታካፍለው ሲያሻህ የምትሄድበት ወዳጅ አለህ?
2. ይንቀኛል፥ ይገምተኛል ሳትል የልብህን የምትገልጥለት ሰው አለህ?
3. በከፋህ ቀን ለመምከር ሳይቸኩል ቁጭ ብሎ በትዕግስት በማዳመጥ የሚያናግርህ ወዳጅ አለህ?
4. በተሳሳትህ ጊዜ ወይም ባጠፋህ ጊዜ ወይም ኃጢአት ስታደርግ አይቶ፥ ይጠላኛል ሳይል የሚገስጽህ ወዳጅ አለህ?
5. በኃጢአት ብትወድቅና ሁሉ ቢከዳህ ብቻውንም ቢሆን ከአንተ ጋር የሚቆም ፥ የማይከዳ ወዳጅ አለህ?
6. እንደ አቶ ሮበርትና አቶ ማርሊ ፥ ኑሮን አብሮህ የሚገፋ የክፉ ቀን ወዳጅ አለህ?
7. ከሰው ሁሉ ጋር የማይካፈሉትን ሚስጢርህን ለወዳጅህ ብትነግረው እንደ ራሱ ነገር አድርጎ ይጠብቀዋል?
8. ከዚህ ከወዳጅህ ጋር ለጸሎትና ለፍቅር ምን ያህል አዘውትራችሁ ትገናኛላችሁ?
9. አንተ ራስህ ለሌላ ሰው ታማኝ ወዳጅ ነህ?

## ወዳጅ (ጓደኛ) ለእኔ የማይሆንልኝ ለምን ይሆን የሚል ጥያቄ ይኖረሃል?

ከአንዱ ወይም ከሁለቱም ወገን ፍቅር ባለመኖሩ ወይም ባለመጠበቁ ነው። ምክንያቱም :-

“ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም ፤ አይታበይም ፤ የማይገባውን አያደርግም ፥ የራሱንም አይፈልግም ፥ አይበሳጭም በደልን አይቆጥርም ፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመፃ ደስ አይለውም ፤ ሁሉን ይታገሣል ፥ ሁሉን ያምናል ፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።” (1ቆሮንቶስ 13፥4-7)

ከዚህ በላይ በተመለከተው ቃል መከበር ወይም አለመከበር ወዳጅ ማግኘት ወይም ማጣት እንደሚያጋጥም አያከራክርም። ከዚህም ጋር የእግዚአብሔር ሰው ፥ ለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ እንደሚጸልይ ጓደኛንም እንዲሰጠው እግዚአብሔር አምላኩን በጸሎት መጠየቅ አለበት።

እነዚህ ጥያቄዎች ጓደኛን ለማግኘት የሚረዱትን ያህል ለመሆንም ይጠቅማሉ። ጓደኞች እያላቸው፥ባለማስተዋል በቸልታ የሚመለከቱ ሰዎችንም ስለሚያነቃቁ ከብዙ አኳያ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ እገምታለሁ። ጌታ ለዳዊት ዮናታንን እንደሰጠ ላንተም ታማኝ ወዳጅ ይስጥህ። አንተንም ለሌላ ሰው ታማኝ ጓደኛ ያድርግህ። አሜን። (the man in the mirro) ከሚል መጽሐፍ ተወስዶ የተዘጋጀ።




መልዓከ

ገብሪኤል

ከጥንታዊ

ኢንሳይክሎፒዲያ

የተገኘ

ስዕል

## መልዓከ ገብሪኤል

መልአከ ገብሪኤል ከመላእክት አለቆች አንዱ ነው። ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የሚላክ መልእክተኛ ነው። ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ለነብዩ ዳንኤል በተገለጸው ራዕይ (በትንቢተ ዳንኤል 8 ፥ 16 እና 9፥ 21) እንደምናነበው:-

በሐዲስ ኪዳን ደግሞ የመጥምቁ ዮሐንስንና የጌታ ኢየሱስን ልደት ለማብሰር በተገለጠ ጊዜ (በሉቃስ ወንጌል 1፥19 እና 26) ተመልክቷል ።

ቅዱሳን መላዕክትን በአጠቃላይ በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊና አፈ ታሪካዊ አመለካከት አለ። አፈ ታሪካዊው ብዙ ሲሆን ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ክፍል (በዮሐንስ ራዕይ 22 ፥ 8 - 9) የሚገኘው ነው። እንዲህ ይላል:-

“ይህንንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ። በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። እርሱም :- እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፥ ከአንተ ጋር ፡ ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር፡የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ።”

ነገር ግን ለእግዚአብሔር መስገድ የሚቻለው በመጀመሪያ የኃጢአት ይቅርታን በመቀበል ብቻ ነው። ይኸውም ኃጢአት በእግዚአብሔር ቅድስና ዘንድ ሊቀርብ ስለማይችል ነው። ኢየሱስ “የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ” ነው።

“አንድ እግዚአብሔር አለና፥በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ፡ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥...” (1ጢሞቴዎስ 2፥5) በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፥ “የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።” (ሮሜ 8፥34)

* * * * * *

## ማስታወሻ

የተወደዳችሁ ወገኖች :- በ1988 ዓም እአአ በምሠራበት ፋብሪካ አብረውኝ የሚሠሩትን የመኪና ዕቃ ማምረቻ ሠራተኞች በወንጌል መድረስ እንደ ሸክም ተሰጠኝ። ወድያው My God Love's You በሚል የአንድ ገጽ መልዕክት በማዘጋጀት ማሰራጨት ጀመርሁ። በሥፍራው የነበሩ ጥቂት የጌታ ልጆች በታላቅ ደስታ በማሰራጨቱ ስለተባበሩ በሦስቱም ፈረቃዎች ሰፊ ተነባቢነት አገኘን። ሰዎችም ጌታን ተቀበሉ ። ተዳክመው ከቤተ ክርስቲያናቸው ርቀው የነበሩ አማኞችም በርትተው ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመለሱ ምክንያት ስንሆን አየን። በዚህ ተግባር የተጋን ጥቂቶችም መሥሪያ ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሳምንታዊ ስብሰባ ጀመርን። በዚህ ውጤት ተደንቄ እያለሁ ነው ጌታ ይህንን የምታነቡትን አገልግሎት ወደ ልቤ ያመጣው። ከእግዚአብሔር ፍቅር ያልነው የዚህ ደብዳቤ ስምም የተወሰደው My God Love's You ከሚለው ጌታ ሲሠራበት ካየነው ስም ላለመራቅ የተመረጠ ነው።

በ1999 አጋማሽ በአቀራረቡ ምንም ያህል ብስለት ያልነበረው የአማርኛ ጽሑፍ በካንሳስ ከተማና አካባቢው በማሰራጨት የዕምነት ርምጃ ጀመርን። ከዚያም ከመላው ሰሜን አሜሪካ አድራሻዎችን ማግኘት ጀመርን። በአሁኑ ጊዜ ወገኖች በስልክ፥ በኢ-ደብዳቤና በካርድ ድጋፋቸውንና ምስጋቸውን በመግለጽ ድካማችን በከንቱ እንዳልሆነ እያሳምኑን ነው። በአገልግሎታችን አንድም ሰው ወደ ጌታ ቢመጣ፥ አንድም ክርስቲያን ቢጽናና ደስታችን ሙሉ ይሆናል።

ከዚህ አንጻር ልናካፍላችሁ የምንፈልገው ሸክም ስርጭታችን በፖስታ ዋጋ ምክንያት መወሰኑን ነው። ለምሳሌ በኢታሊያ፥ በስዊድን፥ በጀርመን፥ በናይሮቢና በኢትዮጵያ የምናደርገው ስርጭት በፖስታው ዋጋ ምክንያት የተወሰነ ነው።

ስለዚህ ይህንን አገልግሎት ጌታ እንዲሳሰበዎ መጠን በጸሎት፥በጽሑፍና በገንዘብ አስተዋጽዖ እንዲደግፉ ለጌታ ክብር እንጠይቃለን። እግዚአብሔር ይባርክዎ።

**********************

በሚቀጥለው እትም አስተያየታችሁን በዚሁ ገጽ ለአንባቢዎቻችን ማቅረብ ስለምንፈልግ፥በጽሑፍ ብትገልጹልን በጣም ደስ ይለናል። ከዚህ በፊት የጻፋችሁልንም ብትሆኑ አሁን ስማችሁን ስለምንጠቅስ ይህን በማወቅ ደግማችሁ ጻፉልን።

ኢየሱስ ጌታ ነው።
ጌታ ይባርካችሁ።
መላኩ ትዕዛዙና ቤተሰብ ።